በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.73
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.73

# የአውሮፓ ህብረት የኢትዮጵያ የባህል ዘርፍን ለማጠናከር 10 ሚሊዮን ዩሮ (260 ሚሊዮን ብር) ለገሰ

የአውሮፓ ህብረት የኢትዮጵያ የባህል ዘርፉን ለማጠናከር 10 ሚሊዮን ዩሮ(260 ሚሊዮን ብር) ለገሰ፡፡

የካቲት 4 ቀን 2006 ዓ.ም. በብሔራዊ ሙዚየን በተከናወነው ስነ ስርዓት የባህልና ቱሪዝም ሚንስትር አቶ አሚን አብድልቃድር እንደገለፁት መንግስት ለባህልና ቱሪዝም ዘርፍ እድገት ከመቼውም በላይ ትኩረት የሰጠ ሲሆን የአውሮፓ ህብረት ዛሬ ያደረገው ልገሳ ይህንን ጥረት የሚያግዝ ነው ብለዋል፡፡

ሁሉም ባለድርሻ አካላት በአውሮፓ ህብረት የተደረገውን ልገሳ በመጠቀም የታሰቡትን ፕሮጀክቶች ለማስፈፀም እንደረባረቡ አደራ ያሉት ሚንስትሩ ህብረቱ ላደረገው ልገሳ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት ስም ምስጋና አቅርበዋል፡፡

በእለቱ "የኢትዮጵያን ታሪካዊ ቅርሶች ልማት" በሚል መሪ ቃል በተደረገው ውይይት የህብረቱ ተወካዮች እንደተናገሩት ህብረቱ የለገሰው ገንዘብ የአምስት ዓመት ፕሮጀክቶችን ለማስፈፀም የሚውል ሲሆን የክልሎችን ባህል ለማጎልበት፣ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ለማከናወን፣ የቅሪተ አካላት መገኛ ቦታዎችን ለመጠበቅና ለማስተዋወቅ፣ እንዲሁም የያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት ለሚያከናውናቸው የሙዚቃ ስራዎች እገዛ የሚውል ነው፡፡

በፕሮጀክቱ 9 ክልሎች የሚታቀፉ ሲሆን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ፣ ጋምቤላና ሶማሌ ክልሎች በተለይ በአቅም ግንባታ እንቅስቃሴው ትኩረት እንደሚያገኙ ለመረዳት ተችሏል፡፡

# የቻይና የንግድ ልዑካን በመጋቢት ወር መጨረሻ ሊመጡ ነው

ቁጥራቸው ከ20 እስከ 25 የሚጠጉ የቻይና የንግድ ልዑካን ከኢትዮጵያ አቻዎቻቸው ጋር የአቻ ለአቻ ውይይት ለማድረግ እና እንዲሁም በኢትዮጵያ ያለውን የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎችን ለማየት በመጋቢት ወር መጨረሻ ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጡ የቻይና የሳይንስና ኢንጅነሪንግ ኮሌጅ ልዑክ ሚስ ኩንግ ዚያ ገለፁ፡፡

ሚስ ዚያ ይህንን የገለፁት በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የካቲት 5 ቀን 2006 ዓ.ም. ከዋና ፀሀፊው አቶ ጋሻው ደበበ ጋር በፅህፈት ቤታቸው ባደረጉት ውይይት ነው፡፡

በዕለቱ ዋና ፀሀፊው ስለምክር ቤቱ አደረጃጀት፣ የሥራ ኃላፊነት፣ ራዕይና ተልዕኮ በዝርዝር ያብራሩ ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት የንግድ ልዑካን የሚመጡበትን ዓላማ ስኬታማ ለማድረግ መንግስት ትኩረት በሰጠባቸው የንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ቢሆኑና በተለይ በኮንስትራክሽን፣ በማዕድን ማውጣት፣ በግብርና ማቀነባበሪያ ላይ ቢሆን የተሻለ ይሆናል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

አድራሻ፡ስልክ፡ - +251-011-5517699
ኢ-ሜይል: ethchamb@ethionet.et
ደረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.73
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.73

የንግድ ልዑካኑ ወደኢትዮጵያ ሲመጡ ከፍተኛ የቻይና የመንግስት የስራ ኃላፊዎች አብረው እንደሚመጡ የተገለፀ ሲሆን በእለቱ ከኢትዮጵያዊያን አቻዎቻቸው ጋር የንግድ ለንግድ ውይይት እንደሚያደርጉም ለመረዳት ተችሏል፡፡

# የምክር ቤቱ የማኔጅመንት አባላት በቅርብ ከተሾሙ ሚንስትሮች ጋር መከሩ

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ፀሀፊ አቶ ጋሻው ደበበና ምክትላቸው አቶ እንዳልካቸው ስሜ ከሌሎች የማኔጅመንት አባላት ጋር በመሆን አዲስ ከተሾሙ ሁለት አምባሳደሮች ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ መከሩ፡፡

የካቲት 12 ቀን 2005ዓ.ም. በምክር ቤቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ የተደረገው ውይይት በብራዚል የኢትዮጵያ አምባሳደር ወ/ሮ ስንቅነሽ እጅጉንና በቱርክ የኢትዮጵያ አምባሳደር አቶ አያሌው ጎበዜ ጋር ሲሆን በጋራ በሚሰሩባቸው በርካታ ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ መክረዋል፡፡

የምክር ቤቱን የስራ ኃላፊነትና ተግባራት በዝርዝር በማስረዳት የጀመሩት አቶ ጋሻው ከአምባሳደሮቹ ጋር ሊሰሩ በሚችሉባቸው በርካታ ጉዳዮች ዙሪያ በተለይ የሀገሪቱን ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማስተዋወቅ በቅርበት መስራት እንደሚገባቸው ተናግረዋል፡፡

ከአምባሳደሮቹ ለቀረበላቸው ዝርዝር ጉዳዮች የምክር ቤቱ የማኔጅመንት አካላትም ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

## ፎቶ ዜና









አድራሻፋክስ: - +251-011-5517699
ኢ.ሜይል: ethchamb@ethionet.et
ደረ-ገጽ:- www.ethiopianchamber.com